# ★ዴሞክራሲያ★

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅጽ 34 ቁጥር 4 ታኅሣሥ 2001 ዓ.ም.


## ታኅሣሥ 40 ዓመት-

## በወጣቶች ትግል ሀገር ይድን

*ከዛሬ 40 ዓመት በፊት በታኅሣሥ ወር ተማሪ ጥላሁን ግዛው በዚያን ጊዜ በነበረው አገዛዝ የፀጥታ ሠራተኞች በማታ ተገደለ ። ይህን የግፍ ግድያ በመቃወም ተማሪዎች ባካሄዱት ሰልፍና የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሌሎች ተማሪዎችም መስዋዕትነትን ከፈሉ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በማያወላዳ መንገድ ከአገዛዙ ጋር መቆራረጥ ብቻ ሳይሆን የነበረውም ትግል ወደ ሌላ ደረጃና ይዘት መሸጋገሩም ግልፅ ሆነ ። ታኅሣሥ ለብዙ ዓመታትም የኢትዮጵያ ሰማዕታት ተማሪዎች ወር ተብሎ ሲከበር ቆይቷል።*

*ከአርባ ዓመት በፊት የጥላሁን ግዛው መሰዋዕት መሆን ታሪካዊ አንደምታና ይዘት የነበረው ነው። በትውልድ ጥላሁን የልዕልት ሣራ ግዛው ወንድም የነበረ ቢሆንም ሰልፉ ከጭቁኑ ሕዝብ ጋር ስለነበር በአገዛዙ ተገድሏል። በወቅቱ ስለነበረው የተማሪ እንቅስቃሴ ዛሬ የሀሰት መረጃ ሊሰጡ የሚሯሯጡ ቢኖሩም ያ ታሪካዊ እንቅስቃሴ ተማሪዎችን በብሔረሰብ ሳይለያይ በኢትዮጵያዊነትያደራጀና ሁሉንም ከመደብ ጀርባ አንፃር ሳይሆን በእምነታቸው ፈርጆ ያታገለ ነበር። ጥላሁን በጥይት እንዲገደል የተወሰነው የተማሪውን እንቅስቃሴ ቅስም ለመስበርና በዚህም እርምጃ ሰቅጠጥ ብሎ ትግሉን እንዲያቆም ነበር። የአፄውን አገዛዝ የተካው ፋሺስታዊ ቡድን ደግሞ በዚሁ መንፈስ ቀይ ሽብርን አካሂዶ የሕዝብን የትግል እንቅስቃሴ ለአንዴም ለሁሌም ሊሰብር ሞክሮ ነበር። ወያኔም በበኩሉ የሕዝብን እምቢታ በሽብርና ግድያ ሊገታ ሲጥር ዓመታትን አስቆጥሯል። ግን የሕዝብን ትግል የማፈኑ ዕቅዳቸው ለሁሉም አልተሳካም። ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ እያለ እየዘመረ ወጣቱ በቁጣ ተነሳስቶ የየካቲት አብዮት ቆራጥ ወታደር ሆነ እንጂ፣ በኢሕአፓም ዙሪያ ተደራጅቶ በቆራጥነት ታገለ እንጂ ተሸማቆ ለባለነፍጦቹ አላደረም። ግድያና ሽብር ሟቾቹን ሳይሆን ቀሪውን ማሽማቀቂያና ከትግል ማራቂያ ነውና የኢትዮጵያ ወጣቶች ለዚህ ሰለባ አልሆኑም። የወጣቱን ሀገር ወዳድና ቆራጥ የትግል መንፈስና ሚና ዴሞክራሲያ በመስከረም 1983 እንደሚከተለው ያቀረበው ገላጭ ይሆናል--*

*“ ተቃውሞን ማሰማት፤ተበድልኩ ብሎ ማንገራገር፤ እንዴት! ብሎ ሥልጣናትን መሟገት፤ ሥልጣንን የሚፈታተኑ ሐሳቦችን መሰንዘር በማይታለምባት፤ሥርዓተ ትምህርቱም ለሥርዓቱ በሚያረግድባት ፊወዳላዊት ኢትዮጵያ ተማሪውና ተራማጅ ምሁሩ የላብ አደሩን፤ የአርሶ አደሩን፤ ባጠቃላይም የሠፊውን ሕዝብ ብሶት በማስተጋባት፤ ጥያቄዎቹን በማሰማት ከተማሪና ከሙያ ማኅበራት ዓቅም በላይ በመንጠራራት የግፉዓን ጠበቃም፤ ሐዋርያም፤ ሰማዕትም ሆኖ የፈፀመው ገድልና ለየካቲት አብዮት ያነጠፈው ጥርጊያ፤ አብዮቱም ከሕዝብ እጅ እንዳያፈተልክ የአብዮት ጠር ሆነው ከች ካሉት ፋሺስታውያን ኀይላት ጋር ያደረገው ግብግብና የከፈለውም ዋጋ በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ውስጥ ራሱን የቻለ በነድ የተፃፈ ምዕራፍ የያዘ ነው፡፡”*

ከአርባ ዓመት በፊት የነበረውን ጨቋኝ ሥርዓት ዛሬም የሚናፍቁና የሚደግፉ፤ ያ የተማሪ እንቅስቃሴ የነበረው ኢትዮጵያዊነት የሚጠናወታቸው ክፍሎች የዚህን እንቅስቃሴ ይዘትና ተልዕኮ አወላግደውና ጥላሸት ቀብተው ለማቅረብ ቢጥሩም፤ በተጨባጩ ሁኔታ ሕግ እንቅስቃሴው የራሱ ድክመቶች ቢኖሩትም በመሠረቱ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የተዋደቁ ወጣቶች ታሪካዊ እንቅስቃሴ መሆኑን ማንም ሊፍቀው የሚችል ሐቅ አይደለም፡፡ የተማሪው እንቅስቃሴ ሚና የፖለቲካ ድርጅት ሚና ሊሆን ባለመቻሉም ወጣቱ ከፍ ወደ አለ ድርጅታዊ ትግል ይሸጋገር ዘንድ በምስጢር የተደራጀው ኢሕአፓ የራሱን ጥረት አድርጎ ውጤት ማስገኘቱም ሌላ የማይካድ ሐቅ ነው፡፡ በየካቲት አብዮት ወጣቱ ከኢሕአፓ ጋር ሆኖ በመታገል ድሉን እንዳይቀማ ቢጥርም፤ ለጥቆም የመጣውን ፋሺስታዊ አገዛዝ በመታገል ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነት ቢከፍልም ሕዝባዊ መሠረት የሌላቸው መኮንኖች በዘመናዊ ባንዶችና በባዕዳን ተረድተውና ነፍጣቸውን ተጠቅመው ከውድቀት ዳኑ፡፡ የማንኛወም ሀገር የነገ ዕጣ መሠረት ወጣቱ ነው፡፡ ብሩህ ተስፋን አቅፎ፤ ከዛሬ ባሻገር ነገ ተነገ ወዲያን ሌላ ጎህን አማትሮ አይቶ ይቻላልን በድፍረት እያዜመ፤ የትግሉ ነው ሕይወቴ ብሎ ለሀገሩና ለሕዝቡ የሚሰዋው ሁሌም በአብዛኛው ወጣቱ ነው፡፡ ወጣቱን ማደራጀትና ማሰለፍ፤ ብሩህ ራዕይ ማስጨበጥ፤ የቻለ ድርጅት የመሪነቱን ሚና ተረክቦ ውጣ ውረዱን ከተወጣ የድል ባለቤትም ሊሆን ይችላል፡፡ የወጣቱ ትግል ለኢትዮጵያ መሠረታዊ ለውጥ ምሰሶው ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ ከጊዜ በኋላ ኢትዮጵያዊነታቸው የተሸረሸረ ጠባቦች ብቅ ብለው የተማሪውን እንቅስቃሴ ቅርስ አፈር አብልተው ግንጠላን ሰባኪ ቢሆኑም የሀገራችን ተራማጅ ተማሪዎች የአበጠው ይፈንዳ የሕዝብ እኩልነት ይረጋገጥ ሲሉ ሁሉም በአንድነት በኢትዮጵያዊነትና ለኢትዮጵያ በሚል ፍላጎት ነበር፡፡ “መሬት ለአራሹ” ሥርዓቱን ያናጋ መፈክር እንደሆነው ሁሉ “የሕዝብ እኩልነት መብት እውን ይሁን” የሚለውም ለከፋፈለህ ግዛው ሥርዓትም የውድቀቱ ደወል ነበር፡፡ የተማሪው እንቅስቃሴ “መሬት ለአራሹ” ብሎ ስር ነቀል ለውጥ ጠያቂነቱን ከማብሰሩ በፊት ተጀምረው የነበሩትን የብሔረሰብና የኤርትራ እንቅስቃሴዎች ይኸው እንቅስቃሴ ፈጠራቸው ሊባል የሚችልም አይደለም፡፡ የተማሪው እንቅስቃሴም ሆነ በ964 ዓ.ም. የተመሠረተው ኢሕአፓ ለችግሮቹ

መፍትኄ ለግሰው የኢትዮጵያን አንድነት በዴሞክራሲ ሊያስጠብቁ ጣሩ እንጂ የመዘዙማ ፈጣሪዎች ገዢዎቹ ነበሩ። ይህን በተመለከተ የግንቦት 1994 ዴሞክራሲያ “ ኢሕአፓ የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ” በሚል ርዕስ ውስጥ የሚከተለውን አቅርቦነበር--

*“ በተለመደው አቀራረብ የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ ተብሎ የሚጠቀሰውን የሕዝብን እኩልነትና መብት የሚመለከተው ዓቢይ ችግር የተከሰተው አንዳንዶች እንደሚሉት በግራ ክንፍ ርዕዮት ያመነው ተራማጁ ምሁር ወይም የተማሪው እንቅስቃሴ ከአፈር አድበልብሎ ወይንም ከአየር ቆንጥሮ እነሆ ጥያቄ ተገኘ ወይንም ተፈጠረ ብሎ ስላመጣው አልነበረም። በወቅቱ የነበረው የአፄው ሥርዓት በሕዝብ መሀል በመደብ፣ በሃይማኖትና በፆታ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በውልደትም--ኋላ ብሔረሰብ በተባለውም የተነሳ--በግልፅ ልዩነት ያደርግ ነበር። በቋንቋውና በማንነቱ ደረጃ የሙሉ ዜግነት ስሜት እንዳይኖረው የተደረገው ሕዝብ ቁጥር ቀላል አልነበረም። ይህ የብሔረሰብ ጭቆና ሊባል የበቃው ሁኔታም በተለይ በደቡቡ ክፍል ከጪሰኝነት ማለትም ከመሬት ባለቤትነት መነፈግና ከምርትም ውስጥ በርከት ያለውን ክፍል ከመገበር ጋር የተያያዘ ስለነበር በቀላሉ የማይታለፍ ነበር። ያም ሆኖ ደግሞ የፊውዳሉን ስርዓት ይታገሉ የነበሩ ወጣቶች ለጉዳዩ የሌለውን ክብደትና የማይገባውን ትኩረት በመስጠት ቅድሚያን አልሰጡትም። የኢትዮጵያ ተማሪ እንቅስቃሴ ሕዝባዊ ትግሉን የጀመረውና ያስተዋወቀው በ “ መሬት ለአራሹ” መፈክር ሲሆን ይህ የተማሪው ትግል እየተፋፋመ በሚሄድበትም ወቅት የኤርትራ እንቅስቃሴ (በጀብሀ አማካይነት)፣ በባሌ በነዋቆ ጉቱ የሚመራውና በሶማሊያ የተደገፈው የትጥቅ ትግል፣ የሜጫ ቱለማ እንቅስቃሴ ወዘተ በመድረኩ ነበሩ። የብሔረሰብ ጥያቄ ሊባል የበቃው ጉዳይ መፍትኄ ይሰጠኝ ብሎ ይጠይቅ ነበር ማለት ይቻላል። ተራማጆቹ ያለን ችግር አይተውና አለ ብለው መድኃኒት በመፈለጉ ተግባር ላይ አተኮሩ እንጂ ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ላይ አልተሰማሩም።”*

የቀድሞ ወጣቶች በብሔረሰብ ሆነ በሃይማኖት አልተለያዩም። በመሀላቸው ልዩነት የተፈጠረው በፖለቲካ አቅዋምና ምርጫ መሠረት ብቻ ነበር። የወያኔ ጠባቦችና መሰሎቻቸውን የማይጠቀልለው ይህ ሂደት ያንን እንቅስቃሴ ክቡር ያደርገዋል። ጊዜ ስላለፈ ግን የታሪክ በራዦች ምስክር የጠፋ እየመሰላቸው የባጡን የቆጡን በሐቅ መልክ እያቀረቡ፣ ወጣቶቹ ለዚህና ለዚያ ሴረኛ ሰለባ የሆኑ አስመስለው በመተረክ ትውልድን ሊያደናግሩ እያጣሩ ናቸው። ወጣቱ ግን ለህገሩና ለጭቁኖች ሲል ውድ ህይወቱን የሰጠ መሆኑን ታሪክ መዝግቦለታል። ለላባደሩና አርሶ አደሩ፣ ለሕዝብ እኩልነት፣ ለድኻው ወገን፣ ለሀገር ሉዓላዊነት ፀንቶ የቆመ ጀግና ወጣት ነበርና ዛሬም ነገም ገድሉ የሚወሳለት ይሆናል። የፋሺስቱ ደርግ ዕልመት ሲጠና የተከተለው ቀቢፀ ተስፋ ወጣቱንም በክሎት የተወሰነው በጥበት ሲጠለፍ፣ ቀሪው ከፖለቲካ ሲርቅ ሌላው ክፍል ደግሞ ፀንቶ ለዓመታት መታገሉ ሊዘነጋ የሚገባው አይደለም። ትላንትም ዛሬም ግን

ወጣቱ ግዴታው ከባድ ሆኖ ይገኛል--ላስተማረው ሕዝብ የሚከፍለው ዕዳ የሚዘነጋ አይደለምና:: ያኔ በመስከረም 1983“ ዴሞክራሲያ” ይህን ግዴታ በሚከተለው መልክ አቅርቦት ነበር---

> *“ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ብዙ ውጣ ውረድን ያለፈ፤ ብዙም ገና የሚጠብቀው እንደመሆኑ መጠን ከታጋዩ፤ ከአገር ወዳዱ የሚጠበቀው ደግሞ በዚያው ልክ የበዛ ነው:: በተለይ የኢትዮጵያ ተማሪ-ምሁር በቀላሉ ተከፍሎ የማያልቅ ዕዳ እንዳለበትም ላንዳፍታ መዘንጋት የለበትም:: ያ ታርዞ ያለበሰ፤ ተርቦ ያበላ፤ አንጀቱን አጥፎ፤ አፈር ገፍቶ ሀገርን ሀገር ያሰኘ፤ በመሐይምነት ተወስኖ የትምህርትን በረከት ያደለ ፤ ጠበብት ሊቃውንት ያስገኘ ፤ ጎስቋላ ሕዝብ፤ ያ ብሶት ዋይታው የወለደውን፤ ጅግኖች ልጆቹ የረገፉበትን አብዮት ተነጥቆ፤ እግር ተወርች ታስሮ፤ አፉን እንደ ጌኛ ተሸብቦ በደይን የሚማቅቅ ሕዝብ ከምሁራን ልጆቹ ብድሩን ይጠይቃል:: ጊዜው በተራዘመ ቁጥር ወለዱም ይጨምርና መክፈልም ያዳግት ይሆናል:: ሆነም ቀረም ምሁር-ተማሪው፤ አገር ወዳዱ የኀሊና ዳኝነት የሚበይንበት ሁሉ መክፈል ያለበት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ዕብሪት፤ ትምክህት፤ ጠባብነት በተባሉ ቸንካሮች ተቸንክሮ ኤሎሄ! ኤሎሄ! እያለ በሚያቃስትበትና የብተና ፃዕረ ሞት ጥላውን አጥልቶበት አንድ ሕዝብ አንድነቱን ጠብቆ፤ እንደ ሀገር ህልው ሆኖ መቀጠሉ እያጠራጠረ በመጣበት ባሁኑቱ አኪት ሰዓት ነው::”*

የኢትዮጵያ ህልውና በወያኔ ለከፋ አደጋ ተጋልጦ ባለበት በአሁኑ ጊዜ በተለይ የወጣቱ ግዴታና ሚና ምንድነው ብሎ መመርመርና ከጨለማው ወደ ብርሃን ለመሻገር ምን መደረግ አለበት የሚለውን ማጤኑ የግድ ይሆናል:: ፋሺስት ኢጣሊያ ሀገራችን ሲወር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ምሁሮችና ወጣቶች ጨፍጭፏል:: ሁሉም አገዛዞች ከነገሬ ቀደም ወጣቱን በጠላትነት ፈርጀው በተቻላቸው አጥቅተውታል:: በተለይ ደርግና ወያኔ የሀገራችንን ወጣት በመምተር ደረጃ ያደረሱት ጉዳት ሰቅጣጭ ነው:: ዛሬ ሀገር ህልውናዋ በጥያቄ ውስጥ በገባበት ሁኔታ የወጣቱ ይዘት አሳሳቢ መሆኑን መደበቁ ለማንም የሚጠቅም አይሆንም:: የኢትዮጵያ ጠላት የሆነው ወያኔ በባዕዳን እርዳታ ለሥልጣን ከመብቃቱ በፊት የትግራይን ወጣቶች በተለይም አርሶ አደሮቹን በፀረ አማራ ቅስቀሳ በክሎና በሀሰት ታሪክ አደራጅቶ ወይም ይል እንደነበረው ጠርንፎ ለጥፋት አሰማራ:: ለሥልጣን ሲበቃ ደግሞ የመላ ሀገሪቷን ወጣቶች በብሔረሰብና ጎጥ ለመከፋፈል ተዋድቆ በከሀዲዎች እርዳታና ትብብር በከፊልም ቢሆን ዕቅዱ ተሚልቶለታል:: ወያኔ በቀደደው የጠባብነት ቦይ የፈሰሱ ደግሞ ወጣቱን በኢትዮጵያዊነት ሳይሆን በጎጥ ደረጃ እንዲሰለፍ በማድረጋቸው ድሮ አንድ ሆኖ የታገለው ወጣት ሊከፋፈል ቻለ :: ይባስ ብሎ ወጣቱን በጎጂ ልምዶችና ሀገር ጥሎ በመውጣቱ “ አማራጭ” በመተብተብ እይታው ወደ ትግል እንዳይሆን ለማገድ በብዙ ሚሊዮን ብር የታጀበ ዘመቻ በመካሄድ ላይ ነው:: በዚህ ዘመቻም ለሥልጣን ያበቁት ባዕዳን ሙሉ በሙሉ እየተባበሩ ናቸው::

ወጣቱ ትውልድ በአውደ ፖለቲካው ግንባር ቀደሙን ቦታ ይዞ ካልተገኘ የፖለቲካ ድርጅቶችም ቢሆን ሊታደሱና ሊጠናከሩ ይከብዳቸዋል። ከዚያም በላይ ትግሉ ሊጠናከር መቻሉ በጣም ያጠራጥራል። ወያኔ ወጣቱን በድርጅትም በጥቅምም በተንኮልም ለመያዝ፤ መያዝ ካልቻለ ደግሞ እርባና ቢስ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ባለበት ሁኔታ ወጣቱን ወደ ሀገር አድኑ ትግል ለመሳብ የሚደረገው ጥረት ወሳኝ ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች ያ ትወልድ በትግል መፈክሮችና በሕዝብ ፍቅር እንደተሳበው ሁሉ ወጣቱን ዛሬ በራዕይም በአርአያነትም ሊስቡ መቻል አለባቸው። የዛሬ ወጣት ሀገሩን እንደሚወድ መስዋዕት ሆኖና ታስሮም ተሰቃይቶም አሳይቷል። የዛሬው ወጣት የሚያታግለው ካገኘ ታሪክ ሊሠራና አኩሪ ምዕራፎችን ሊያፅፍ የሚችል መሆኑ አያጠራጥርም። ለዚህ ግን ያሉትን ጋሬጣዎች አስወግዶ መገኘት አስፈላጊ ነው። ወጣቱን ሊስብ የሚቻልና ከግለኝነት ይልቅ ሕዝባዊነትና ሀገር ወዳድነት መሻሉን የሚያሳምን ራዕይ ሊሰፍን መቻል አለበት። የምሁራን በሊኅ አዕምሮ ከግል ወደ ወል፤ ከራስ ጥቅም ወደ ወገን ፍቅርና የሕዝብ ጥቅም፤ ከስደት ወደ ሀገራችን ዱርና ጫካ በፋኖነት ለመሰማራት ይመርጥ ዘንድ መሪህ ነን የሚሉትም ተዓማኒነት ሊኖራቸው ይገባል። ዛሬ ታጋይ ነገ ከወያኔ መንደር አውድልዳይ፤ ዛሬ ጀግና ነን ባይ ነገ ግን ሁናቴው ጠጠር ሲል ሽብረክ ባይ ሆነው ከተገኙና ቃላቸውና ተግባራቸው ከቶም የማይገናኝ ከሆኑ ሌላውን ሊስቡ ቀርቶ የተጠጋውንም ያሸሻሉ። የዚያ ትውልድ የትግል ወኔ እንዲያ ጠንካራና አስደናቂ የሆነው የትግሉ መሪዎችንም ቆራጥነት ከነ ተሰፋዬ ደባሳይ እስከ ኢንጂኔር ኦስማን፤ ከስዩም ከበደ እስከ ማርቆስ ሀጎስ ወዘተ... አይቶ ነው ቢባል ትክክል ነው። ጀግናን የሚያፈራው ጀግና ነውናም ወጣቱ ጀግኖችን ማየት አለበት፤ ተከትሎ በጀግንነትና በፅናት እንዲታገል። ማለትም ድርጅቶች የራሳቸውን ድክመት አስወግደው በገቢር ሲታገሉ ከታየ ወጣቱ ይከተላቸዋል፤ ይደግፋቸዋል። የዚህም ሐቅነት በ1997 ዓ.ም. በገሀድ መታየቱ ብቻ በቂ ምስክር ነው።

ከዚህም አንፃር ባበዕድ ሀገር ያለውም ወጣትና ምሁር አወቅኩ መጠቅኩ ብሎ በአጓጉል መኩራራት ወይም ድርጅቶችን እያናከሱ ትግሉን መጉዳት ሳይሆን አዎንታዊ አስተዋፅዖ ማድረግ ይጠበቅብታል። ይህን በተመለከተ ኢሕአፓ ከዛሬ 18 ዓመት በፊት በዴሞክራሲያ የፃፈው ማሳሰቢያ ዛሬም ወቅታዊ ሆኖ ይገኛል።

> " *በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን የምዕራቡ ዓለም በሚሰጠው ዴሞክራሲ በመጠቀም፤ በኢትዮጵያዊ ፖለቲካዊ፤ ኤኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊ፤ ባኅላዊና ታሪካዊ ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያሉ ጥናቶችና ምርምሮችን በማካሄድ፤ የኢትዮጵያ ነባራዊ ችግሮች በተገቢ ገፅታዎቻቸውእንዲታዩ መፍትሔያቸው በዚሁ አኳያ እንዲያስተነትን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ያስተማራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸከማቸው ዕዳ ነው። መፅሀፉ እንዲህ ይላል፤ እንዲያ ያዝዛል፤ እንዲግ ይሠራለታል፤ እንዲያ አይሠራለትም፤ እየተባለ እንደ ቃለ እግዚአብሔር የሚነበንብበት፤ እንደ በቀቀን የሚንጣጣበት፤ አሜን ያለ አማኝ*

*ተብሎ ሞገሥ የሚያገኝበት፣ የጠየቀ የመረመረ ፣ መናፍቅ ተብሎ ለኩነኔና ለውርጅብኝ የሚዳረግበት የፖለቲካ ዘይቤ መዳረሻውን፣ ያስከተለውን መዘዝና ሰቆቃው፣ ያፈለሰውን ሀገር፣ ያነገሰውን ንብረት አሁን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ቅልጥጥ አድርጎ አሳይቶናልና ወደዚያ ተመልሶ ዳግመኛ መዳከሩ ቢያንስ የሞኝ ፈሊጥ ይሆናል:: በጥራዘ ነጠቅነት መክነፍን፣ በሌጣ ትርጉም መጋለብን፣ እንዳፈተተ መቆንፀልን ለማስቀረትና በዚህም ምክንያት የሚፈጠረውን የተሳከረ ሂደትና መመሳቀል ፈር፣ አቅጣጫ ለማስያዝ፣ ፖለቲካዊ ትንታኔዎች አየር ላይ መጥቀው በሕዝብ አናት ላይ የሚበሩ ሳይሆኑ ወረድ ብለው ከሕዝቡ ወዝ ጠረን ጋር እየተዛመዱ፣ የሕዋሳቱን ንዝረት የሚያሰሙ፣ ስሜቱን በትክክል የሚተረጉሙ፣ ምኞቱን የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑና የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ እድገት ደልዳላ መሠረት ላይ እንዲዋቀር ከማድረግ አኳያ የምሁሩ ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም::”*

የኢትዮጵያ ግማሽ በላይ ሕዝብ ወጣት ነው:: ይህን ኃይል በትግል ማሰለፍ ካልተቻለ ድል የቀረበች አይደለችም:: ሴቶች በቁጥር ከጠቅላላው ግማሽ ሕዝብ ናቸወና እነሱንም አደራጅቶ ያላታገለ የድል ባለቤት ሊሆን አይችልም:: ወጣቱ መደራጀት አለበት ብቻ ሳይሆን ሊደራጅም ይችላል:: የዛሬን የፍርሀትና የክህደት ፖለቲካ በዋናነት ወሰዶ ሳይሆን የታጋይ ወጣት ትውልድን ታሪክ አንግቦ አዲስ ታሪክ ሊፅፍ ሊነሳ ይችላል:: በወጣቱ ትውልድ ላይ ተስፋ መቁረጥ ማለት በሀገርና በነገ ብሩህ ቀን ላይ ተስፋ ቆርጦ ወደ ጨለማ መግባት ነውና ይህ አማራጭ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም አይሆንም:: ከጥላሁን ግዛው እስከ ሽብሬ ደሳለኝ ብዙ ሺ ወጣቶች ለሀገራቸው ደማቸውን አፍሰዋል:: የወያኔ ቡትቶ “ ዴሞክራሲ ” ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑን ወጣቱ ለመገንዘብ ጊዜ አልፈጀበትምና የዚሁ አገዛዝ የአፈና ኃይልና የባዕዳንም ሴራ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ እንደማይችል፣ ሕዝብ ቆርጦ ከታገለ ወያኔ ተኖ ጠፊ መሆኑን እንዲያምንበት ያስፈልጋል:: ለዚህም የተጨባጭ ትግል አርአያዎች፣ ስለ ትግል በቃል የሚያነበንቡ ብቻ ሳይሆኑ እየተሰዉና መከራ እየተቀበሉ የሚያስተምሩ ጀግኖች ያስፈልጋሉ:: ከሁሉም በላይ ግን ወጣቱ ኢትዮጵያዊ ለከፋፊዮችና ጠባቦች ሰለባ እንዳይሆን ከፍተኛ ትግል መካሄድ አለበት፣ የሀገር ታሪክ፣ የሕዝብ የጋራ ተጋድሎ መነገር መታወቅ ይገባዋል:: ኢሕአፓ ወጣቱን ዛሬም ወደ ትግል እየጠራ፣ የትግል ቅርሱን ተቀብሎ፣ የሀገር ሰንደቅ ዓላማን አንግቦ፣ በህብረትና በጋራ ከመታገል ሌላ ምንም የሚያኮራ አማራጭ የለም ይላል:: ስለዚህም ዛሬም እንደ ትላንቱ የወጣቱና የምሁሩ ሀገር አድን ተልዕኮ ግልፅ ነውና የኢትዮጵያ ወጣቶች ግዳጃቸውን ለመወጣት ዝግጁ ሆነው መገኘት ይጠበቅባቸዋል::ተቀዳሚው ተግባርስ ምንድነው? የመስከረም 1983 ዴሞክራሲያ ካቀረበው የተለየ መልዕክት የለንም---

“ *በዚህም ሁኔታ ተቀዳሚው ተግባር የመፍትሔውም ዋናው ክፍል ያረመመው ምሁሩ ተማሪው አገር ወዳዱ በውጭ ያለው በሀገር ቤት ካለው ጋር እየተሻተተ ዴሞክራሲያዊ ባህልን ለመዘርጋት የሚያስፈልገውን ርብራብ በመጣል ላይና ልብ*

*ለልብ የሚገናኝባቸው አውታራት በመዘርጋት ላይ ማድረግ ይሆናል። ለዘላቂ የሕዝቦችና የሀገር ጥቅም፣ለዘላቂ የሕዝቦች አንድነት ሥምረት ለዘላቂ ሰላምና ለሉል ዓላማዎች ከፍተኛ ቦታ ሰጥቶ በጋራ መሠለፍ፣ ሊሸጋሽጉ የሚችሉ አቋሞችን ማሸጋሸግ ከዴሞክራሲያውያን ይጠበቃል። ወደዚያ ለመራመድ ለጊዜው አቀበቱ በበዛበት ሁኔታ ግን ቢያንስ የገዛ እምነትን ለራስ ይዞ ያንን እያስተማሩ፣ እየቀሰቀሱ፣ በዚያው እያደራጁ የሌላውን ድርጅታዊ ነፃነት ጠብቆ፣ ልዩነትን በፀጋ ተቀብሎ ከድንፋታና ከፀብ አጫሪነት ታቅቦ፣ ሲቻል የአመራር ኃላፊነት የሚጠየቅውን ግብረገብነትና ጨዋነት ይዞ መገኘት ቢያንስ ግን ሕዝብ በነፃነት ያለምንም ተፅዕኖ ያሻውን፣ ይበጀኛል የሚለውን እንዲመርጥ እምነቱን እሱ ላይ መጣሉ በዴሞክራሲ ፍኖት ላይ የረፋድ ጉዞ መጓዝ ማለት ነው።"*

እነ ጥላሁን ግዛው ከ አርባ ዓመት በፊት የደም ዋጋ ከፍለው ያስተላላፉልንም መልዕክት የኢትዮጵያ ወጣቶች ሀገራቸውን ከጥፋት ለማዳን መታገል ግዴታቸው ነው የሚል ነው።

ወጣቱ የሕዝባዊ ትግሉ አካልና መሪ ነው!
ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!